ቤ/ን

325

የሰ/መ/ቁ. 31682

መጋቢት 12 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ኤጀንሲ

ተጠሪዎች፡- 1. ዘላለም ይልማ ባልቻ

2. መሠረት ይልማ ባልቻ

3. አዳሙ ይልማ ባልቻ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የዚህ ክርክር መነሻ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ከወረዳ 5 ቀበሌ 23 አስተዳደር እና አቶ ፊይሣ ቦንሣ ከተባሉት ግለሰብ ጋር ባደረጉት ክርክር በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ ቁጥራቸው 308 እና 309 የሆኑትን ቤቶች በአ/ቁ. 47/67 መሠረት መወረሣቸው በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል ቤቶቹ ለተጠሪዎቹ ይመለሱ ሲል የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ይህ ተከራካሪ ባልሆንኩበት የተሠጠው ውሣኔ እንዲነሣ ሲሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358ን ጠቅሰው በመቃወም ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልክተዋል፡፡ አመልካቹ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሐምሌ 17 ቀን 1998 ዓ.ም. ጽፈው ያቀረቡት ማመልከቻ ይዘት ሲጠቃለል ቁጥሩ 309 የሆነው ቤት በአ/ቁ. 47/67 መሠረት በትርፍነት የተወረሠ ሲሆን አመልካቹ በአ/ቁ/2/1995 አንቀጽ 46/1/ መሠረት ቤቱን እንዲያስተዳድር ስልጣን ተሠጥቶታል በመሆኑም ተጠሪዎች /የስር ከሣሾች/ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ባላቀረቡበት ሁኔታ ቤቱን እንዲረከቡ የተሰጠው ውሣኔ መብቴን የሚጎዳ በመሆኑ ሊነሣ ይገባዋል የሚል ነው፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የአመልካቹን ተቃውሞ እና የተጠሪዎቹን መልስ መርምሮ በጥቅምት 3 ቀን 1999 ዓ.ም. በመ/ቁ. 21594 በሰጠው ፍርድ በመቃወም አመልካች ቁጥሩ 309 የሆነውን ቤት ለማስተዳደር መብት ያለው መሆኑን ያላስረዳ በመሆኑ ፍ/ቤቱ በጥር 15 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ሊነሣ የሚገባ ሆኖ አላገኘውም ሲል ተቃውሞውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኙት አመልካች አቤቱታቸውን በይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካቹም የስር ፍ/ቤቶች ተቃውሞውን ውድቅ ማድረጋቸው አ/ቁ. 47/67ን በሚገባ ያልመረመረና ያላገናዘበ በመሆኑ ቁጥር 309 የሆነው ቤት ለተጠሪዎች እንዲመለስ የተሠጠው ውሣኔ በውሣኔ እንዲሻር ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሐምሌ 2 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ ጠይቀዋል፡፡ ይህም ችሎት የአመልካቹን የሠበር አቤቱታ መርምሮ ክርክር የተነሣበት ቤት በአ/ቁ 47/67 መሠረት ለመወረሱ ማስረጃ አልቀረበም በሚል ቤቱ ለተጠሪዎች እንዲመለስ መወሰኑ አግባብ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲል ተጠሪዎችን አስቀርቧል፡፡ የሰበር ተጠሪዎችም ለአመልካች አቤቱታ በሐምሌ 30 ቀን 1993 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቹም አቤቱታውን በመልስ መልሱ አጠናክሮ ቀርቧል፡፡

ይህም ችሎት የግራ ቀኙን ክርክርና የሥር ፍ/ቤት ውሣኔዎችን በጥሞና መርምሯል፡፡ እንደተመረመረውም ከሁሉ አስቀድሞ ምላሽ የሚሻው ጭብጥ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቀድሞውንስ ቢሆን በዚህ ጉዳይ የቀረበለትን ክስ ተቀብሎ የማከራከር ስልጣን ነበረው ወይ? የሚለውን ነጥብ መሆኑን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በወረዳ 5 ቀበሌ 23 አስተዳደር ጽ/ቤት እና በአቶ ፊይሣ ቦንሣ ላይ ያቀረቡት ክስ ተከሣሾቹ በአ/ቁ. 47/67 ያልተወሰነበትን ቁጥራቸው 308 እና 309 የሆኑት ቤቶች አላግባብ ስለያዙብን ለቀው እንዲያስረክቡን የሚል ነበር፡፡ የአሁኑ የሰበር አመልካችም ሆነ በስር ፍ/ቤት ተከሣሽ የነበረው የቀድሞው ወረዳ 5 ቀበሌ 23 ጽ/ቤት ለክርክሩ መንስኤ የሆኑት ቤቶች በአ/ቁ. 47/67 ተወርሰው የሚያስተዳድራቸው መሆናቸውን በመግለጽ ተከራክረው ያንም የስር ፍ/ቤት ቤቶቹ ስለመወረሣቸው የሚያረጋግጥ ተገቢው ቦረበም በሚል ቤቶቹ ለአሁን ተጠሪዎች እንዲመለስ በማለት ወስኗል፡፡ በመሠረቱ አዋጅ ቁጥር 47/67ን መነሻ አድርጎ አላግባብ የምርጫ ቤቱ ተወስዷል በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን አዋጁን ለማስፈጸም ለተቋቋመው የሚኒስቴር መ/ቤት በኩል እየተመረመሩ ተገቢውን ውሣኔ ማግኘት ያለባቸው ስለመሆኑ በአዋጁ ተመልክቷል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ የምርጫ ቤቴን በቀላጤ፣ በቃል ትዕዛዝ ወይም በመመሪያ ከሕግ ውጭ ተወስደብኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርበው መወሰን እንደሚገባቸው በሕጉ ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ ክፍሎች የሚሰጡ የባለቤትነት ማስረጃዎችን መሠረት አድርገው በሚቀርቡ የባለሃብትነት ጥያቄዎች ላይ ፍ/ቤቶች እንደነገሩ ሁኔታ ስልጣን ከሚኖራቸው በቀር ተወርሰዋል ተብለው በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ስር ያሉ ቤቶች ይመለሱልኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መሠረት አድርገው ፍ/ቤቶች የቤቱን መወረስና አለመወረስ ለማረጋገጥ ማስረጃዎች መርምረው የሚደርሱባቸው መደምደሚያዎች ለፍ/ቤቶች በሕግ ያልተሰጣቸው ስልጣን ከመሆኑም ባሻገር የአስፈፃሚ አካላቱን ስልጣንና ተግባር በግልጽ የሚቃረን ነው፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ክርክር በተነሣባቸው ቤቶች ላይ ከአስፈፃሚ አካላቱ የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ባላቀረቡበት ሁኔታ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች በአ/ቁ. 47/67 መሠረት ትርፍ ናቸው ተብለው ለመወረሣቸው መቅረብ ይገባው የነበረው ቅጽ 003 በወረዳ 5 ቀበሌ 23 ጽ/ቤትም ሆነ በአሁኑ አመልካች አልቀረበም በሚል ቤቶቹ አልተወረሱም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡



## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪዎች አግ ሁ አስፈፃሚ አካላት የባለቤትነት ማስረጃ ባላቀረቡበት ሁኔታ በሕግ ባልተሰጠው ስልጣን ቤቶቹ በአ/ቁ. 47/67 ተወርሠዋል ወይስ አልተወረሱም የሚለውን ነጥብ መርምሮ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡
2. ይህ ውሣኔ ተጠሪዎች በቤቶቹ ላይ አለን የሚሉትን መብት አግባብ ላለው አካል አቅርበው ከመጠየቅ አያግዳቸውም፡፡
3. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በጥር 15 ቀን 1998 ዓ.ም. በመ/ቁ 21594 የሰጠው ውሣኔ የቤት ቁጥር 309 በተመለከተ ብቻ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በጥቅምት 13 ቀን 1999 ዓ.ም. በመ/ቁ 21594 ቁጥር 309ን በተመለከተ ብቻ የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡
5. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም. በመ/ቁ. 50128 ቁጥር 309ን በተመለከተ ብቻ የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ